


ኦገስት 10 ቀን 2009 ዓ/ም

# የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቺካጎ መቋቋሙን አስመልክቶ የተሰጠ መግለጫ

በኢትየዮጵያ ሕዝብ አርበኞች ግንባር ስር ተደራጅተው፣ የሚገኙ ጀግኖች አርበኞች ያለ መስዋትነት ነጻነት እንደማይገኝ ገና ከጅምሩ የተገነዘቡ በመሆናቸው፣ ለኢትዮጵያ አንድነትና ነጻነት ክቡር ህይወታቸውን አሳልፌው በመስጠት ህዝባዊ መሰረቱን በማጎልበት ግንባሩን ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ላይ በማድረስ ለሕዝባችን ታላቅ የነጻነት ተስፋ ሆነዋል።

በመሆኑም ነጻነት ወዳድ የሆንን በአሜሪካ፣ ቺካጎ ነዋሪ የሆንን ኢትየዮጵያኖች ኢሕአግ የደረሰበትን የእድገት ደረጃና የሃገራችንን ወቅታዊ ተጨባጭ ሁኔታ መሰረት ያደረገ ተከታታይ የስልክ ስብሰባዎችን ከኢሕአግ የአለም አቀፍ የውጭ ጉዳይ ድርጅት ሃላፊ ጋር በማድረግና የጋራ መግባባት ላይ በመድረስ፣ በመመሪያው መሰረት ለጀግኖች አርበኞች አስፈላጊውን ድጋፍ ሁሉ ለማድረግ ዛሬ ኦገስት 10 ቀን 2009 ዓ/ም የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቺካጎ ማቋቋማችንን ይፋ ስናደርግ በታላቅ ደስታ ነው።

በዚህ አጋጣሚ በቺካጎ የምትገኙ ኢትዮጵያኖች በሚከተለው ኢሜል አድራሻችን
ከኛ ጋር በመገናኘት ለግንባሩ አስፈላጊውን ድጋፍ ታደርጉ ዘንድ ጥሪያችንን እናቀርባለን።
ኢሜል አድራሻችን; eppfchicago@gmail.com

**አንድነት ኃይል ነው!!**

**የኢሕአግ ድጋፍ አስተባባሪ ኮሚቴ በቺካጎ**